# “አፍንጫ ሲመታ ዐይን ያለቅሳል”

እጅግ አላስፈላጊ የሆነ የወንድማማቾቹን ደም እንደጎርፍ ያፋሰሰው የሀገራችን ምድር ቁራጭ ክፍል የሆነው ባድመ፤ ዛሬም እንደገና ትንግርቱን አስጎስሟል። የእውነት ሀገር አድን ጥሪ መስሏቸው ውድ ህይወታቸውን አሳልፈው በሰጡ ሰማእታት ጀግኖች ተጋድሎ በሀገሪቱ ግዛት ውስጥ ላለፉት አስራሰባት ዓመታት ተጠብቆ የቆየው ቦታ በአሁኑ ሰዓት በድንገት ለተሸናፊውና የንጹሃንን ደም በከንቱ ላፋሰሰው አካል በነጻ መቸሩ አጠያያቂ ሆኗል። በዚህ አሳፋሪ ድርጊት የጀግና እናት ምን ይሰማት ይሆን ብሎ መጠየቅ የሚገባ ይሆናል። ብዙዎቻችንም በሀገሩ ሉዓላዊነትና የዳር ድንበሯ ጉዳይ በድፍን ታሪኩ በአይበገሬነት የሚታወቀው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህን የኩታራ ሥራ ምን ትርጉም ይሰጠው ይሆን ስንል እንደመማለን። ነገሩ የያዛትን ቆቅ ለቆ በቅዝምዝም ሊጥል እንደሚሻ የተጃጃለ ልጅ ጨዋታ አይነት ነው። ወይስ ሚስጥሩ “ውስጡን ለቄስ” ይሆን? መጠርጠር አይከፋም። መልካም እንመኝና፤ እንዲህ ልግሥናው ከሰፈነ፤ በጌምድር ሰሜንና ወሎ ክፍለሀገሮች በጉልበት የተነጠቁት አንጡራ መሬታቸው ይመለስላቸው ይሆን? እንዲህ ከሆነ እውነትም ሰላም በኢትዮጵያ ሰማይ ላይ እያንዣበበች ነው። ወይስ አሁንም በተስፋ እያገሳን ሣር ሣሩን እያየ ገደል እንደገባው በሬ ራሳችን እያታለልን ነው? አለ ነገር እንጠርጥር። በአሁኑ ወቅት ዶ/ር አብይ አህመድ የሀገሪቱ ባለተራ መሪ ሆነው ብቅ ባሉበትና በየአደባባዩ በጫሩትና ባባበሉን ትልቅ ተስፋ ሕዝቡ መልካሙን ሁሉ እየተመኘ ለአብሮነትና ለሰላም በጎመዠበት ጊዜ ውስጥ ባድመን ተሽቀዳድሞ የማሸሸቱ ጉዳይ ቀዳሚው የቤት ሥራ የሆነባቸው ለምን ይሆን?  ዝግ ብሎና ጊዜ ሰጥቶ ስለመፍትሄውና አፈጻጸሙ መስዋእትነት ከከፈለው ሕዝብ ጋር መነጋገርና የማያዳግም ምላሽ መስጠት ሳይሻል ይቀራል ትላላችሁ? ነገርን ነገር ያነሳዋል እንዲሉ፤ ይኸ የስሞኑስ በመንግሥት ታግረው የቆዩ ትልልቅ ተቋሞችን ወደ የግል ባለሃብትነት የማስተላለፉ ጉዳይ ከልብ የታሰበ ይሆን? ከህብረተሰቡ ውስጥ እነማን ናቸው በአሁኑ ሰዓት እነዚህን አንኳር አንኳር የኢኮኖሚ አውታሮች በአክሲዮን መግዛት የሚችሉትና ቋሚ ሃብታቸው ማድረግ የሚችሉት? የተጀመረው የአንድነት ተስፋ መሬት ላይ ከሚመተረው ወርድና ስፋት ጋር እንዳይጣረስ ማስተዋልና መመርመር ይገባል ይሆናል።

የሀገራችን ኢትዮጵያ ሉዓላዊንትና ሰላም እንዳይረጋገጥ “ራዕይ” የታዬላትና በፈጠራ የተከበበችው ባድመ፤ ዛሬም ጊዜ ጠብቃ በድንገት ያለ ሕዝብ ይሁንታ እንደዋዛ መሸኘቷ የጤና አይደለም። ‘ባለራእዩ መሪ” በህይወት ሳሉ ሌት ተቀን ያሰቡትና ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ እንቅልፍ አጥተው የታተሩት ከኢትዮጵያ መፈራረስ ማግሥት ጠንካራ የሆነች ምሥራቅ አፍሪቃዊት ሀገር መመሥረት ለመሆኑ የድካማቸው ውጤት የተሟላ መረጃ ነው። በሀገራችን ኢትዮጵያ ላለፉት ሃያ ሰባት ዓመታት የተካሄዱትን ፖለቲካዊ፡ ኢኮኖሚያዊ፤ ዲፕሎማሲያዊና ማህበራዊ ክንውኖች ለተመለከቱና ላጤኑ ታዛቢዎች፤ ሊጠይቁት የሚያስገድዳቸው ነገር ቢኖር፤ ለምንድን ነው በዚች ሀገር ውስጥ ትልቅ ሃላፊነት የተሸከሙ ባለሥልጣናት የሚያከናውኑት ጉዳይ ሁሉ ያላዋቂና የጠላት ሥራ የሚመስለው? የሚለው ይሆን ይሆናል። ለጥያቄው የተሟላ መልስ የሚሰጣቸው ወያኔ ከልቡ ኢትዮጵያን ሊገነባ አልተዘጋጀም ነበር፤ ምኞቱ ሌላ አዲስ የህልም አገር መመሥረት ነበር። ለአብነት ያህል እንዲህ ለማለት ምን እንዳስደፈረ የሚከተሉትን ዋና ዋና ክንውኖች እንመልከት፡

፩ኛ) ሀገሪቱ ተፈጥሯዊ የባህር በሯን እንድታጣ ወዳጅ ታዛቢዎቻቸው ግራ እስኪገባቸው ድረስ ፈቅደውና ባርከው አስረከቡ፤ ዓላማቸው በህልማቸው ለምትታያቸውና ሊገነቧት ላሰቧት ሀገር የባህር በር እንድትሆን ማመቻቸታቸው ነው፡

፪ኛ በህገ-መንግሥት ደረጃ ከፋኝ ያለ ሁሉ ኢትዮጵያዊነቱን ወርውሮ በመጣል በወደቀችው ሀገር ላይ ከቻለ የየራሱን ነጻ አገር ሊያቋቁም የሚችልበትን፤ አለዚያም በአዲሲቷ ሀገር ጥላ ሥር ሊያሳድረው የሚችል አንቀጽ ደነገጉ፤

፫ኛ) መታወቂያው ኢትዮጵያዊ መልኩና ዜግነቱ ሳይሆን ጎሳው እንዲሆን ታስቦ በነቂስ በኪሱ ይዞት የሚዞር የማንነቱ መታወቂያ ካርድ ተዘጋጀለት፤ ይህም እሳቱን ሲጭሩት ጎራ ለይቶ እንዲተላለቅ ምቹ ሁኔታ መፈጠሩ ነው፤

፬ኛ) ለአዲሲቱ የህልም ሀገር የተሟላ ቅድመ ዝግጅት ለማድረግ ሰሜን ጎንደርን አካሎ እስከ ጎጃም ዘልቆ የዓባይን ወንዝ እስከመቆጣጠር የደረሰ ስልታዊ እቅድ ተይዟል፤ በዚህም የቅድመ ዝግጅት መስፋፋት የመጀመሪያ እርምጃ ከበጌምድር ሰሜንና ወሎ የተነጠቁት ለምና መጋቢ አካባቢዎች ያለ ሕዝብ ፈቃድ ወደ ትግራይ እንዲጠቃለሉ ተደርጎ ሙሽራዋ “ቢኒሻንጉል” ነገና ተነገ ወዲያ ከኢትዮጵያዊነቷ ጋር ተፋታ ለአዲሲቷ አገር ምሥረታ ስትሞሸር ቤተሰብና ሠርገኛ ሁነው እንዲቀበሉ ተመቻችቷል። በዚህ ስልታዊ አከላለል ለምና አምራች ቦታዎችን መንጥቅ ብቻ ሳይሆን፤ ኤርትራ በጎንደር በኩል ከመሃል ሀገር ጋር የነበራትንና ሊኖራት የሚችለውን በር በመዝጋት ኤርትራና መሃል አገሩ ሊገነኙ የሚችሉበት የኢኮኖሚ፤ የድህንነትና የመረጃ ጥቅሞች ልውውጥ በአዲሷ ሀገር መሪዎች በኩል በሚጠየቅ ፈቃድ ላይ ብቻ እንዲሆን የታቀደ ይመስላል፡

፭ኛ) ኢትዮጵያዊነትን በሚገልጹ የሥነ-ልቦና እሴቶችና ተቋሞች ላይ በመዝመት የማዳከም ርብርቦሽ ተካሄዷል፤ ዜጎች ባልባሌ ባህልና ባህርይ እንዲበከሉ ቁጥጥር አልባነት ነግሶ ልቅ ሆኗል፥

፮ኛ) የሀገሪቱ አስተዳደር በዘርና በቋንቋ እንዲከፋፈል ተድርጎ ዜጎች እርስ በርሳቸው እንዳይግባቡና አንዱ ሌላውን እንዲጠልፍ ተመቻችቷል፤ የጋራ ባህልና የጋራ ሥነ-ልቦና እንዲጥፋ፤ ኢትዮጵያዊነት እንዲዳከም በር ቀዳጅ ሆኗል።

፯ኛ) የአዲሷ ሀገር ምሥረታ ዋልታ የሆነቺው ትግራይ ልጆቿ ከትግርኛ በተጨማሪ በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች እንዲማሩ ተደርጎ ለመጭው ዘመንና ተተኪ ትውልድ ግልጋሎት በብቃት ሲዘጋጁ ፤ ሌላው ክፍል አትድረስብኝ ተባብሎ በየራሱ ብሄረሰብ ቋንቋ ብቻ ጠቦና ተሰብስቦ እንዲቀመጥና ለነገዎቹ ምጡቅ ባለሃብቶችና ምሁራን የደለበ አገልጋይ እንዲሆን ተደላድሏል፤

፰ኛ) ቋሚና ተንቀሳቃሽ የሆነ ሃብትና የልማት አውታር ለአንድ አካባቢ ትኩረት ተሰጥቶት ወደዚያው እየተከማቸ፤ ሌላው ክፍል በተሳትፎው እንደ ሁለተኛ ዜጋ ቶቆጥሯል፥

፱ኛ) ለታሪኩ አባዎራ የሆነውን የትግራይ ሕዝብ በሽርፍራፊ ጥቅማጥቅምና መርዛማ በሆነ የፖለቲካ ስልት ከሰፊው ወገኑ ጋር ሆድና ጀርባ እንዲሆን ያለመታከት ተሥርቷል; ይህም ለነገ ለተጠነሰሰው የፍርሻ ተንኮል ደም በማቃባት አብረን ልንኖር አንችልም ወደሚል ድምዳሜ መግፋትና በቀላሉ ዓላማን ለማስፈጸም የተሸረበ ሴራ ነው፤ ሐውዜን ልብ ይሏል።

ከዚህ በላይ የሰፈረው አብነት የሚጠቀስበት ምክንያት ዛሬ እንደገና አነጋጋሪ የሆነው የባድመ ጉዳይ ይኸን ከመሰለው እርጉም ዓላማ ጋር የተሳሰረ መሆኑን ለማመልከት ነው። ከአስራ ሰባት ዓመት በፊት የኤርትራ መሪዎች ዓይናቸውን ወደ ትግራይ ሲያቀኑና ይገባናል ያሏትን ባድመን ለመቆጣተር ሲያኮበኩቡ፤ ነገሩን የደረሱበት ብዙዎቹ የሕወሓት መሪዎችና ተወላጆች ሁኔታው አሳስቧቸው ተነጋግረውበት እንደነበር በወቅቱ ተገልጿል። ይሁን እንጅ “ባለ ራእዩ” መሪያቸው አቶ መለስ ዜናዊ  እውነቱን ሆዱ እያወቀው ጉዳዩን አጣጥሎና ሟርት አስመስሎ የሥራ ባልደረባዎቹን በመገሰጽ ባድመን ለሚፈልጓት ጊዜ ሰጥቶ እድትጠቃ ሆነ። ይህ አካሄዱ በብዙዎቹ ዘንድ ጥርጣሬ አሳድሮ አቶ መለስ ምርጫው በፖለቲካውና በህይወቱ አጣብቂኝ ውስጥ ገብታበት ነፍሱን አሳድሮ ለማያምንበት መተባበር ግዴታው ሆነ። እንደዚህም ሆነና የኤርትራን ጥቃት ለመከላከል በተከፈተው አንገብጋቢ ጥያቄ እምነቱን እንደያዘ የአብዛኛውን አቋም ተግባራዊ ሊያደርግ ተስማማ። የመንግሥት ባልደረቦቹም የመሪያቸውን ጉዳይ በይደር ይዘው ቅድሚያ ትኩረታቸውን ከኤርትራ ጋር ለሚደረገው ፍልሚያ አደረጉ።  “ከኤርትራ መልስ ወደ መለስ” የሚል የሕዝብ ዜማም በጦርነቱ ዝግጅት ወቅት በስፋት ተስተጋባ። ከብቁ ዝግጅትና የሞቀ ሀገራዊ ወኔ ጋር ኤርትራን ለመቅጣት ጦርነቱ ተጀመረ። እንደተጠበቀው የሻቢያን ምሽግ ለመስበርና ተንደርድሮ ለመዋጥ የሚያስችለውን አቅም ለማሳየት ጊዜ አልወሰደም። ሰፊው የእትዮጵያ ሕዝብ ምንም እንኳ ሁለቱ ጥጋበኞች በአባትና እናታቸው ሀገር ላይ የፈጸሙት ደቫ አሳዝኖት የቆየ ቢሆንም፤ የኤርትራ መሪዎች በቀረችው ሀገሩ ላይ ወረራ ፈጸሙ ተብሎ የተነገረው ጉዳይ ግን የድፍረት ድፍረት ሆኖ ስለተሰማው ያለማመናታት ወደ ጦር ሜዳ ተመመ። ጦርነቱ እንደተጀመረና የሻእቢያ መከላከያ እየተመታ ሲያፈገፍግ ታላላቅ የዓለም አቀፍ መገናኛዎች ታሪካዊ ይሁንታ በመስጠት “ኢትዮጵያ ተፈጥሯዊ የባህር በሯን እስከማስመለስ ጦርነቱን ትገፋለች” እያሉ የጦርነቱን ቀጣይነትና የመጨረሻ ውጤት በሚተነብዩበት ቅጽበት ውስጥ እነ መለስ ዜናዊ የአልጀርሱን ድርድር አመቻችተው በመቋጨት በቀጭን ተዕዛዝ ውጊው እንዲቆም አዘዙ። አታላዩ መሠሪ ምክንያት ከባድመ በላይ ውጊያውን ብንገፋ  ከዓለም አቀፉ ማህበርሰብ እንነጠላለን፤ እድላችን እንዘጋለን እርዳታ አናገኝም.... የሚልና የመሳሰሉት ነበሩ። የአቶ መለስ ትልቁ ዓላማው ግን ጦርነቱን የሚመራ እየመሠለ ለአንዴና ለሁሌም ለእርሱ አደጋ የሆኑበትንና ዓላማውን ሊያደናቅፉ የሚችሉትን ጓደኞቹን ማስወገድ ነው። እናም ጦርነቱን ለማወጅ ባሳየው ማቅማማትና ተጎታችነት ሊወቅሱትና የሥነ ሥራአት እርምጃ ሊወስዱበት የሚመኙትን ጓደኞቹን ሳይቀድሙት ቀድሞ የንድፈ ሃሳብ ጦርነት በመክፈት ጥላት ከቀባቸው በኋላ በአመች ጊዜና ቦታ ላይ ከሥራቸውና ከማዕረጋቸው አስፈነጠራቸው። እየተቀላጠፈም በሥነ ልቦና ጦርነትና በዕስር ቅጣት አቅመ-ቢስ አድርጎ ፍጹም አምባገነንና ጨካኝ ሰው ሆኖ ገነነ። የትግራይ ተወላጆች የሆኑትንና ለትግራይ ከልብ የሚቆረቆሩ ባለሥልጣኖችን እየመነጠረ አባሮ፤ ጎብጠው በሚታዘዙትና በአመለካከታቸው እርሱን  በመሰሉ፤ አንድ እግራቸውን ኤርትራ ላይ በተከሉ፤ ኢትዮጵያን አቃጥለው አዲስ አገር ለመመሥረት በሚናፍቁ መናፍቆች ተከበበ። “ባለ ራእዩ መሪ” የተባሉትም ከዚህ በሁዋላ ነው። ዛሬም ድረስ ያለው ዋና ችግር ይኸው አቶ መለስ ዜናዊ ተክሎት የሄደው መርዝ ነው፤ ዶ/ር አብይ በከፈቱት እንጭላንጭል ወደ ውስጥ ስንመለከት ከጀርባ ቁጭ ብለው ሲዶሉቱ የምናያቸው ኢትዮጵያን የማይወዱና ሊያጠፏት የወሰኑ ሰዎች ናቸው።

ብዙ ጊዜ ሲባል እንደቆየው የሕወሓት የጥፋት ፕሮግራም የመጨረሻ ውጤቱ በክፉም በደጉም ተፋቅሮና አንድነቱን ጠብቆ የኖርውን ሕዝብ ማቃቃርና ማለያየት ነው። የሕወሓት መሪዎች ከርኩስ አመለካከታቸው ራሳቸውን ነጻ ሳያወጡ የትግራይ ነጻ አውጭ ነነ እያሉ በትግራይ ሕዝብ ስም ብዙ ጸያፍ ነገር ሠርተዋልና ለረዥም ጊዜ ሊጎዳው የሚችል የኪሳራ እዳ ጥለውለት ሊሄዱ ይችላሉ። ይሁን እንጅ ካለፈው አጭር የመከራ ጊዜ ይልቅ ብሩህ ተስፋ ሊታይበት የሚችለው መጭው ረዥም ዘመን ይበልጣልና በስሙ በሀገርና በታሪክ ላይ የደረሰውን በደል ተገንዝቦ በቃ በማለት ድምጹን ካሰማ ምን ጊዜም ጥቃቱን የማይወደው ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጎኑ እንደሚቆም በሙሉ ልብነት መናገር ይቻላል። የትግሉ ግብ ኢትዮጵያን የማይወዱና የማይወክሉ ከሥልጥናቸው ተወግደው በዜጎቿ የከበረች ዴሞክራሲያዊት ሀገር ማጽናት ነው።

የሕወሓት መሪዎች በትግራይ ሕዝብ ስም ለእኩይ ዓላማቸው ስኬታ ሲሉ ከፈጸሟቸው እኩይ ተግባሮች አንዱ የጎንደር መሬት ታሪኩና ነፍስ ሥጋው የሆነውን ወልቃይት ጠገዴን ያለአባቱ ወደ ትግራይ ማጠቃለላቸው ነው። ይህ ድርጊታቸው ዛሬ የትግራይ ሕዝብ ባድመን አጥቶ እርር ድብን እንደሚለው ሁሉ ጎንደሬዎቹንም እጅግ አስከፍቷል። ለነገሩማ የቀዬ ጉዳይ ሆኖ ጎንደሬዎች ተጠቀሱ እንጅ የወልቃይት ጠገዴ ጉዳይ ቢያንስ በሦስት ምክንያቶች የሁሉም ኢትዮጵያዊ ጉዳይ ሊሆን የሚገባው ነው። ይከውም ፩ኛ) የሕወሓትን የአዲስ ሀገር ምሥረታ ህልም በእንጭጩ ለማስቀረት የኢኮኖሚያቸው እምብርት ሊያደርጉት የፈለጉትን ወልቃይት ጠገዴን መንሳት ያስፈልጋል፡ ፪ኛ) ደጋውና መስኩ የጎንደር ሰፊ መሬት የማምረት አቅሙ እየደከመና የሕዝብ ቁጥር እየተጫነው በመምጣቱ የክፍለ ሀገሩ የወደፊት የኢኮኖሚ ዋስትናው ሰሜናዊ መዕራብ ይዞታው መሁኑ እርግጥ ነው። ስለዚህም ይህ ህብረተሰብ ተራቁቶና ደህይቶ ለጥገኝነት መዳረግ ስለማይኖርበት መብቱና ይዞታው ሊጠበቅለት ይገባል፤ ያለውና የተረፈው በውዴታው ያካፍላል እንጅ በጉልበታም ሊነጠቅ ስለማይገባው ማለት ነው። ፫ኛ) በጎንደር በኩል ከኤርትራ ጋር ሊኖር የሚገባውን የእሴትና የኢኮኖሚ ፍሰት የሕወሓት መሪዎች ሊፈጥሯት በሚሿት አዲስ ሀገር  ከልለው የደኅንነትና የገበያ ልውውጥ ችግር ሊወልዱ ስለሚችሉ ኢትዮጵያዊያን በትጋት ሊታገሉት ይገባል። ይህ እንግዲህ “አምሐራ” የሚሉትን የህብረተሰብ ክፍል ለማጥቃትና ዘሩን ለማጥፋት ካላቸው ጥኑ ፍላጎት ጋር አብሮ የሚጤን ነው።

እርስ በርሳችን እንደጋገፍ ሲባል የአንዱን መብት ሌላኛው አክብሮና ጠብቆ ሲገኝ ነው። ስለዚህም አንዱ ወገን በእራሱ ላይ ሊደርስ የማይፈልገውን በሌላው ላይ እስካላደረገ ድረስ መተባበር ተፈጥሯዊ ይሆናል። ዛሬ የትግራይ ሕዝብ ጥያቄ ሲያነሳ እንደትላንቱ አድማጭና ሞቅ ያለ ትብብር የማያጣው በእሱ ስም በብዙሃን ወንድሞቹና እህቶቹ ላይ የተፈጸመውን በደል ነውር ነው ሲል ነው።  ላለፉት ዓመታት በመላ ሀገሪቱ የተከሰተው ከፍተኛ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ እንዲሁ ለፈንጠዝያ አልነበረም፤ ብርቱ የሆነ ሀገራዊ ችግር በመኖሩ ነው። ይህን ችግር ደግሞ ሁሉም በአንድላይ ካልተሰማው በአጭር ጊዜ ውስጥ መፍትሄ አያገኝም። መንቃት የጀመርነው ዛሬም ቢሆን “የት ነበራችሁ” መባባሉን እንተወውና ከእንግዲህ በሁዋላ ላለው “ውሾን የወደደ ውሾ” ተባብለን እርስ በርሳችን ተደጋግፈን ከቆምን መንገዱ ጨርቅ ይሆናል።

ከአክብሮት ጋር፤

የዉልሰው አፈረ